# ትግራይ ለደ/ር አብይ....

# ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ለመሆን ጊዜው አሁን ነው

### ማ. ፍቅር 7-21-18

ላለፉት አመታት ለተነሳው አመፅ ትክክለኛ መንስኤው መርምሮ እና አመዛዝኖ ለመናገር የሚከብድ ነገሮች ያሉ ቢሆንም ነገር ግን ስር መሰረቱ ድህነት መሰረት ማድረጉ ጥርጥር የለው፡፡እርግጥ ነው አመፁ በተለያዩ ፍላጎት በላቸው አካላት እና ግለሰቦች እየተመራ በተለይም በኦሮሚያ የፍትህ ጥያቂ ፣ የፖለቲካ ጥያቄ በሚመስል መንገድ ረዘም ላሉ ወራት ተንሰራርቶ ነበር፡፡እውነታው ግን ሀገራችን ገና በድህነት ስር ላይ በመሆና  የስራ አጥነት ፣ የችግር ፣ በአጠቃላይ የመጠማት እና የራብ ስሜት በፖለቲካ ሽፋን አድርገን መጠየቃችን ነው፡፡እንግዲህ ከሁሉም በላይ ሰላም መሰረት ነው፤ ሰላም ካለ ሰርቶ ስለመብላት ይታሰባል ፣ ሰርቶ መብላት ከተቻለ መኖሪያን የማደላደል ፍላጎት ይመጣል፤ የመኖሪያም ፍላጎት ስናሳካ አከባቢ ላይ የመደመጥ እና የመከበር ፍላጎት ይመጣል፤ የመደመጥ እና የመከበር ፍላጎት ሲሳካ ቀጣዩ ፍላጎታችን ሀገር ላይ መክበር እና መከበር ይቀጥላል እንዲህ እያለ በመጨረሻ ለሌሎች ሰዎች መኖር እንጀምራልን፡፡ይህም ስለ መናገር ነፃነት ፣ ስለ የትም ቦታ ሂዶ የመኖር የመስራት ነፃነት እናስባለን እንፈልጋልን፡፡

ስለዚህ አንድ ስራ ያጣ ወይም የፈታ፣ ስራ ለማግኘት ይጥራል የዕለት ጉርሻውን ለማግኘት ይለፋል ፤ታድያ በዚህ ሂደት እንደቻለው ስራ ማግኘት ካልቻለ እንዲሁም የዕለት ምግቡን መሙላት ካልቻለ፤ ሰው በባህሪው ያማርራል እና መጀመሪያ ከሁሉም በፊት ለፈጣሪው ይለምናል ብሎም ያማርራል፡፡ቀጥሎም ለመንግስት እየወረደም ለቤተሰቡ በመጨረሻ ራሱን ይወቅሳል፡፡

በተቃራኒው የሚያስቡ ጢቂት ሰዎች ይኖራሉ ተብሎ ቢታሰብም በአብዛህኛው ግን የመሰረታዊ ፍላጎት አለመሟላት መሰረት ተደርጎ ነገር ግን በሌላ ጥያቄ ሽፋን ተሰጥቶት የተነሱ ጥያቄ እና አመፅ ነበር፡፡

ከፋፍለን ለመመልከት ያክል፡

**በአማራ ክልል፡-**



ለማንኛውም አስተያየት በአዲሚኑ ኢሜል መስጠት ይቻላል፡

አማራ ክልል ላይ የተነሳው አመፅ በዋነኝነት የዲሞክራሲ ችግር አለ ሳይሆን የደንበር ጥያቄ መሰረት ያደረገ ነበር፡፡አሁንም ቢሆን እንደዚህ አይነት ጥያቄ በተለይም በትግራይ ጠረፍ እና በአማራ ጠረፍ መካከል አለ፡፡

የደንበር ጥያቄ እንደ አንድ ኢትዮጵያ ሲታሰብ መነሳት አልነበረበትም፤ ምክንያቱም **ኢትዮጵያ ውስጥ ለኢትዮጵያውን ደንበር ፤ ክልል የሚባል ነገር የለም** ፡፡ ምክንያቱም ሁሉም አገራችን በመሆኑ ነው፡፡ይሁን እና ጥያቄ በግንዛቤ ዕጥረት ቢነሳ መነሳት ያለበት ጥያቄው የተነሳበት ቦታ ነዋሪዎች ነው እንጂ የሌላው ህዝብ አይደልም፡፡

መሬቱ የእኛ ነበር የሚባል አስተሳሰብ አሁንም ቢሆን ገዳይ ነው፡፡ምክንያቱም መሬት **የብሄሮች ሳይሆን የሀገር በመሆኑ ነው**፡፡አይ ተሳስታሃል መሬት የብሄር ነው ካላችሁኝ ደግሞ መልሱ አይ መሬት ከዚህ ቀደም የነገስታት ነበር ስለዚህ ቀድሞ የነገሰው እዚህ አገር የመሬት ይዞታው በጣም ሰፊ ስለነበር ፍትህ ይሰጥ ካልን በቅርብ ለነበሩ ነገስታት ሳይሆን መስራቾች ነገስታት መሰረት በማድረግ መሬት ክፍፍል ላይ እንገባለን ማለት ነው፡፡

ስለዚህ **የአከባቢው ነዋሪ የያዘውን መሬት ራሱ ሊኖርበት ይገባል**፤ አለበለዚያ የአማራ ብሄር በሀገሪቱ በሙሉ ተበታትኖ ይገኛል ስለዚህ የሚኖርበት አከባቢ መብት ሊያገኝበት አይችልም ማለት ነው፡፡በመሆኑም ሁሉም በያለበት በሰላም እንዲኖር ከዚህ አይነት አስተሳሰብ መውጣት አለብን፡፡

**የኦሮሞ ክልል፡-**

የኦሮሞ ህዝብ ሰፊ የህዝብ ቁጥር ያለው እና ሰፋ በላ የኢትዮጵያ ክልል የሚኖር ህዝብ ነው፡፡በክልሉ ባለፉት አመታት የነበረው ችግር በዋነኝነት **ጥላቻ መሰረት ያደረገ** ህዝብን ያፈናቀለ ፤ የሰው ሂይወትም እንዲያልፍ መሰረት የሆነ በመጨረሻም የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር ወደ ስልጣን እንዲመጣ ያደረገ ሰፊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ነበር፡፡

ጥላቻ መሰረት ያደረገ ሲባል አንድም ባለፉት ነገስታት ለብሄሩ ይሰጥ የነበረ ክብር ዝቅተኛ በመሆኑ ለሁሉም በሚባል መልኩ ተመሳሳይ ነበር፡፡ ይህንን በሰፊው ተጠቅመውበት አሁን ከለው መልካም አጋጣሚ ይልቅ በተለይም ወጣቱ ለድብቅ አላማ ማለትም **ኦሮሚያ ብቻ** የሚል ድብቅ ተልዕኮ እንዲወስዱ በማሳመን እና በማታለል ብዙ መሰረተ ልማት በማወድም የሌላውን ህብረተሰብ በማፈናቀል እንዲሁም በመግደል እዚህ ደርሰዋል፡፡



ለማንኛውም አስተያየት በአዲሚኑ ኢሜል መስጠት ይቻላል፡

በመጨረሻም የአሄዴድ አመራር የወጣቱን ፍላጎት ለመቀልበስ ይሆን ወይም ተቃውሞን ራሱ ይምረው ግራ በሚያገባ መልኩ **የቀሮ አመስጋኝ ሁኖ ጨረሰ ፡፡**

በመቀጠልም ቁሮም የሚታየው አላማውን አሳካ ደ/ር አብይ አህመድ ወደ ስልጣን መጣ ፤አሁን የተረጋጋ ይመስላል፡፡

**ኦሮሚያ ላይ የነበረው ፍላጎት ወደ ጥላቻ አድጎ ለውጡን ካቀጣጠለ በኋላ የተገኘው ሰላም በደ/ሩ ንግግር ወደ ፍቅር ከተቀለበሰ እውነት መልካምነቱ ከምንም በላይ ይፈለጋል፡፡**

እውነታው በክልሎቹ የተነሱት አመፅ መንሴአቸው ከላይ የተጠቀሰው ሁኖ እያለ ወደ ህወሓት የሚሳበበው አላስፈላጊ ትችት ሽፋን ለመስጠት የሚጠቀሙበት አደገኛ አካሄድ ነው፡፡

ህወሓት ለዚህ አገር ሌላው ስራ ይቅር እና እንዲህ ጠያቂ ትውልድ እንዲፈጠር የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡**ይህን ማመስገን ይገባል፡፡**

ምክንያቱም **ህወሓትን ማመስገን ያልቻለ ፍቅር ፤ ህወሓትን ይቅር ያለላ ፍቅር የውሸት ስለሆነ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ** በከፈለው መስዋዕትነት የተረጋገጠው ሰላም የተፈጠረው ንቁ ትውልድ መልሶ ራሱን ለአመታት በልቷል፡፡በአጠቃላይ የትግራይ ህዝብ አሁን ምርጫው ትግስት ነው፡፡ዘመን ይቃያየራል ሌላ ጊዜ ተለዋዋጭ ነው እና የትግራይ ህዝብን ለከፈከው መስዋዕትነት የሚያመሰግን ትውልድ ደግሞ ይፈጠራል፡፡

ለውጡ በዚህም ሆነ በዛ የኢህአደግ መሪውን እንዲቀይር አድርጎ **የመጣው መሪ ከአንደበቱ ብዙ ፍቅር እና ጥላቻ የማይመስል ጥላቻ እየወጣው** ለአብዛሀኛው የአማራ እና ኦሮሞ ህዝብ ደስታን ፈጥሯል በተለይም **ለከተማው ህዝብ፡፡**

በተቃራኒ የትግራይ ህዝብ ላይ ተፅዕኖ እየፈጠረ ቢገኝም፡፡

እንግዲህ ሁሉም ምክንያቶች አመፅ ለማንሳት እና ለመቃወም በቀላሉ ህዝብ ልብ ላይ ሊገቡ ቢችሉም **መሰረታዊ ችግሩ ግን ድህነት ነው፡፡**

ድህነት ብዙ ግዜ ሰርቶ ከማግኘት ጋር ስለሚገናኝ ህብረተሰቡ ድህነትን ለመዋጋት ይጥራል እንጂ ያን ያህል ለአመፅ እና ለእርስ በርስ ጦርነት አያጋልጥም፡፡ነገር ግን ዋናው ምክንያት ይረሳ እና በዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች ጥያቄ መሰረት በማድረግ አመፅ ለማቀጣጠል ቀላል በመሆኑ ሰው ይመርጠዋል፡፡

**ትግራይ፡-**

የትግራይ ህዝብ ሰፊ እና ለሺህ አመታተ የኢትዮጵያ መሰረት ማዕከል ከመሆን በዘለለ አሁን ላለችው ኢትዮጵያም ቢሆን ከፍተኛ **የህይወት መስዋዕትነት ከፍሎ እዚህ ያደረሰ ህዝብ ነው፡፡**

የሚገርመው ህዝቡ የሚኖርበት አከባቢም ቢሆን ከየትኛውም ኢትዮጵያ ክፍል ለወተደራዊ ስትራቴጂ አመቺ እና በቀላሉ ሊደፈር የማይችል አስገራሚ ቦታ የሚኖር ህዝብ ነው፡፡

ህወሓት በመሪነት የትግራይ ህዝብ አንቀሳቅሳ ታግላለች በትግሉም አሸናፊ በመሆን **ኢትዮጵያ ውስጥ ተበታትኖ የነበረ ማንነት አንድ አንድሆኑ በማድረግ** በውጤቱም አማራ ፣ ኦሮሞ የመሳሰሉት ትልልቅ ብሄሮች እንዲሰባሰብ እና በአንድ መዋቅር እንዲጠረነፍ አድርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ባለፉት አመታት በነበረው አመፅ እና ተቃውሞ ዋንኛ ተጠያቂ የነበረው የትግራይ ህዝብ ነው፡፡እርግጥ ነው ሌላው ህብረተሰብ የትግራይ ህዝብን እነዲጠላ ምክንያት የሆነው የህወሓት ባለስልጣናት የእውነትም ሰሩ አልሰሩ በተለያዩ መንግስታዊ ቁልፍ ቦታዎች መሪዎች ስለነበሩ ነው፡፡

በግሌ ትግሉን መርተው እስከመጡ ድረስ ከሌላው ሰው በተሻለ ደረጃ ስልጣኑም ቢይዙ ምንም ክፋት የለውም ምክንያቱ መሪዎቹ እነሱ ስለሆኑ ነው እርግጥ ነው አዲስ ነገርም አይደለም ምክንያምቱም የትም አለም ላይ መሪ የሚያምነውን ሰው ነው አጠገቡ የሚሾመው፡፡

**ደ/ር አብይም ቢሆኑ እኮ ስልጣኖች ሁሉ ወደ ብሄር ተኮር እያደረጉት እንደሆነ** ማንም መመስከር ይችላል፡፡ታድያ ይህ አከያየድ ለህወሓት ሲሆን ትክክል አይደለም ለደ/ር አብይ ሲሆን ልክ ነው የሚያስብል ምንም መሰረት የለንም፡፡

ዝርዝሮ የተሾመው ሰው የሰራውን ስራ መሰረት ተደርጎ ቢገመገም በብቃቱ ቢሾም ትክክለኛው መንገድ መሆን ያለበት ይመስለኛል፡፡

ለማኝኛውም እውነት ለመነጋገር **የትግራይ ህዝብ በ27 ዓመታት ውስጥ ለ3 ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል፡፡**

- በትግሉ ልጆችን መስዋዕት አድርጓል፣
- በሌሎች ብሄር ጉዳት ደርሶበታል፣

- በጣም የሚገርመው በህወሓት በድርጅቷ ሳይሆን በህወሓት ባለስልጣናት በልጆቹ ነፃነት ተነግፋል፣ታፍኗል በጠቃላይ ተጎድቷል፡፡

የህ ሁሉ እየሆነ ግን የትግራይ ህዝብ አሁንም ጉዳቱን በውስጡ ይዞ የሚሆነውን በመመልከት ከማመፅ እና ከተቃውሞ ራሱን አግልሎ እያየ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ በተለይም በሙሉ ኦሮሚያ እና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ተቃውሞ እና አመፅ መሰረቱ ድህነት እና ጥላቻ ናቸው፡፡ዲሞክራሲ መብቶች መሰረታዊ ናቸው አይደሉም ለሚለው ጥያቄ እርግጥ ነው ፤ አከራካሪ ቢሆንም እንደ አገር ግን መጀመሪያ የዕለት እንጀራ በልተን የምናድርበት ዋስት፣አምሽተን የምናድርበት ቤት እና ልብስ ሲኖረን ወደ ሌላው መልካም ነገሮች እንሸጋገራለን፡፡

አሁን ግን እየሆነ ያለው አብዛሀኛው ህብረተሰብ የሚበለ የሚጠጣ እንደልብ ባለገኘበት ሁኔታ ስለ ድህነት ማስወገድ ስራ ከመስራት ይልቅ ሌሎች ጠቃሚዎች ግን ደረጃቸው ሁለተኛ የሚቀመጡ ነገሮች ላይ ስንባለ እና ስናባላ እንኖራለን፡፡

የማይካድ አንድ ነገር አለ እሱም ማንኛውም ነገር በተሰበሰበ ቁጥር ጥንካሪው እየጨመረ በመምጣት እና የመፈረካከስ ሁኑታው እየቀነሰ ስለሚሄድ ኢህአደግ ብሄሮች መከለሉ ከፊት ከነበረው **የኢትዮጵያውነት ስሜት ወደ ክልላዊ አስተሳሰብ** እንዲሄድ የራሱ ሚና አለው፡፡

**ነገር ግን ህብረተሰቡ በየአቅጣጫው መሳሪያ ይዞ የተነሳበት አላማ ብሄሩ እንዲሰባሰብ እና በቋንቋው እንዲናገር ብሎም እንዲዳኝ መሆኑን ደግሞ መዘንጋት የለብንም፡፡**

ታድያ እንደ ኢትዮጵያ በድህነት ያሉ አገራት ፌደራሊዝሙ ብሄር ተኮር አድርጎ ማዋቀር የራሱ የሆኑ ተግዳሮቶች አሉት ፡፡ ላለፉት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረው ጥላቻ አይነት አስተሳሰቦች ሊያስከትል ይችላል፡፡ለዚህ ግን መፍትሄው ከድህነት ራስን ማውጣት ነው፡፡ድህነትን ያሸነፈ ሰው ምንግዜም አሳቡ ስራየን እንዴት ላስፋፋው ፣ የት ቦታ አዲስ ድርጅት ልክፈት፣ ለሀገሪ ዕድገት ምን ሚና ልጫወት ወዘተ አይነት መልካም አስተሳሰብ ያሳድጋል፡፡ድህነትን ያሸነፈ ማህበረሰብም ቢሆንም የተሻለ አገልግሎት የሚሰጠውን ነጋዴ ድርጅት እንዲመጣለት ይፈልጋል፡፡

ምንም ኬሚስትሪ የለውም ያደጉ የበለፀጉ አገሮች ፌደራሊዝምን የሚከተሉ አገሮች አሉ፡፡እነዚህ አገሮች ቀርቶ የራሳቸውን ዜጋ ይቅርና ከአፍሪካ እና መሰል አገራት የተሰደዱ ሰዎችን ተቀብለው በሰላም እያኖሩ ይገኛሉ፡፡

**የእኛ ችግር አወቃቀሩ ላይ አይደለም መሰረቱ ድህነት ስለሆነ** እምንበላው እና እምንጠጣው ስናጣ ሌሎች ሰዎች ላይ እናደርገዋለን፡፡

## ኢትዮጵያ ላይ ለተከሱቱ ችግሮች ዋና ዋና ምክንያቶች

**ጥላቻ/ዘረኝነት**

**የደንበር /የመሬት ጥያቄ**

**ለላይኛው ምክንያት የሆኑት**

**ስለ ኢ./ያውነት አለማመን**

**እኛ እያለን ሌላው ሰርቶ እንዴት ይለወጣል/ምቀኝነት ጠባብነት**

**እኩል ተጠቃሚነት አለመኖር ተብሎ ስለሚታመን**

**አንድነትን የሚያጠናክር በቂ ስራ አለመስራት**

**ያለፉት መንግስታት ጭቆና/መከፋፈል የፈጠረው ጠባሳ**

**ድህነት**

**ከግንዛቤ እጥረት**

**ለምን እንዲህ ታሰበ**

**ለምን ድህነት በዛ**

**ደህነት ስለበዛ**

**በድንብ መስራት የአቅም ማነስ ስላለ/ድህነት**

**የተሳሳተ ግንዛቤ መበራከት**

**አለመስራት/ ስራን መምረጥ/**

**በቂ የተማረ ህብረተሰብ አለመኖር/ማህይመነት**

ከላይ እንደተመለከትነው ዋናው አብሮ እንዳኖር እያደረገን ያለው **የዘር ጥላቻ ነው**፡፡ለዚህ ምክንያት ደግሞ የመሬት ወይም የደንበር ጥያቄ ወይም ፍላጎት ተከትሎ ከዘመናት በፊት አንዱ በየትም የነገሰ ሁሉ ደንበሩን ለማስፋት የሚሄድበት መንገድ ከተቆጣጠረው በኃላ የሚያስተዳድርበት መንገድ አነሰም በዛ በእያንዳንዱ ብሄረሰብ ተፅኖ አሳድሮ በድምሩ እዚህ ደርሷል፡፡

አንድ አንዱ ብሄር የእውነትም ተጨቁኖ ስለኖረ ኢትያጵያውነት እየጠሩ ነገስታት የእውነትም ተፅዕኖ ስላደረሱ በጅማላ ነገስታትን ከመጥላት የመነጨ አሁን ያለው ህዝብ እንዲጠላ ምክንያት ሁነዋል፡፡

አንዱ አንዱ ደግሞ ራሱን እንደ ተጨቆነ ቆጥሮ ኢትያጵያውነት ከሚለው ትልቅ አስተሳሰብ ወርዶ በመጥበብ የብሄሩን መጠሪያ እንደ አገር እየቆጠሩት ሌላው ህዝብ ጋር ሊዋሀዱ አልቻሉም፡፡

ግንዛቤ እጥረቱ እንዳለ ሁኖ የሌላን ብሄር ህብረተሰብ ወደ ማፈናቀል ፣ መግደል የገቡ ብሄርቶኖች ዋንኛ ምክንያታቸው የግንዛቤ ዕጥረት እና የሀገር ስሜት የፈጠረው ጠባብነት ሲሆን በአጠቃላይ ግን የስርዓት አለበኝነት መጓደል ሌላው ምክንያት ነው፡፡ስርዓት የሚፈጠረው **ከማህበረሰብ(መንግስት) + ከሀይማኖት ትምህርት** ሲሆን በዋነኝነት የማህበረሰብ ሚና ከሃይማኖት ስርዓት ይመነጫል፡፡

ስለዚህ ሃይማኖት አልባነት ወይም በቂ መልካም ስነ ምግባር በማህበረሰቡ ካላደገ የሌላን ህብረተሰብ ክብር እና ሞገስ እንዲሁም መቆርቆር መረዳዳት ላይ አይደረሰም፡፡

ቀስቱን ወደ ታች ባደረግን ቁጥር ምክንያች እየሰጠን በሄድን ልክ የድህነት ሚና እየጎላ ይመጣል፡፡

**እንግዲህ በአሁኑ ጊዜ ሰው አብሮ በሰላም ለመኖር + ለመተጋገዝ + ለመተዘዘን የሃይማኖታዊ ስነ ምግባር /ግብረ ገብነት / በሁሉም ህብረተሰብ ላይ መገለጫው ካልሆነ ድህነትን ማሸነፍ ቁልፍ ነገር ነው፡፡**

**ታድያ ምንድነው የሚሻለው ብለን ከጠየቅን**

አብዛህኛው ህብረተሰብ ሰርቶ መብላት ሳይሆን ሰርቆ መብላት ይፈልጋል፡፡ ሰርቆ ሲባል የግድ ከቁስቁስ መስረቅ ማለት አይደለም፤ ጌዜን ከምንሰራበት ቦታ እንሰርቃለን፣የሰውን አስተሳሰብ እንሰርቃለን፣የተፈጥሮን ሰዓት እንሰርቃለን ራሳችን በራሳችን ከትክክለኛው አስተሳሰብ እንሰርቀዋለን ወዘተ፡፡

**ስለዚህ ስርቆት ማቆም አለብን የመጀመሪያ መፍትሄ፡፡**



ለማንኛውም አስተያየት በአዲሚኑ ኢሜል መስጠት ይቻላል፡

**ዋናው ነገር መንግስት ህዝብን መቀለብ አይችለም፤ስለዚህ እንደ ወታደር ለቀጣዩ ትውልድ ራሳችንን መስዋዕት ማድረግ አለብን፡፡**

ራሳችንን መስዋት ሳናደርግ ሁልጊዜ የምናማርር ከሆነ ልጆቻችን ከድህነት ፣ ከጥላቻ እርስ በራስ ከመባላት አይወጡም ፡፡ለዚህም ነው በተቻለን መጠን ራሳችንን ለቀጣዩ ማህበረሰብ ሲባል ከማማረር፣ ተኝቶ ከመብላት ፣ ከሌብነት እንዲሁም ከጥላቻ ነፃ አድርገን እንደወታደር ሂይወታችን ለቀጣዩ ትውልድ ሲባል መስዋዕትነት መክፈል ያለብን፡፡

እንግዲህ ፍቅርን መሰረት አድርገን ስናወራ **ፍቅር ከሁሉም በላይ ነው**፡፡የሰው ፍቅር ሰውን ያስከብራል ፣ የሀገር ፍቅር መስዋዕትነት ያሰጣል፡፡

የትግራይ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ እውነታውን የተረዳለት ህብረተሰብ ቁጥር ሰፊው የገጠር ህዝብ (የተረሳው ህዝብ) ቢሆንም የከተማው ወጣት ግን በአብዛህኛው የተሳሳተ ግንዛቤ አለ፡፡

ደ/ር አብይ አህመድ በጥላቻ ፖለቲካ ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን መሪነት ቢመጣም ቃላቶቹ ወርቅ ናቸው፣ንግግሩ አየር አይገድባቸውም ጉልበትም አላቸው፡፡የመሪነት ብሃሪያት በግልፅ ታይቶበታል፡፡

- **ደ/ር አብይ አህመድ የኢህአደግ ውጤት ናቸው፣**
- **ደ/ር አብይ አህመድ ላለፉት ዓመታት በወሳኝ ቦታዎች የኢህአግ መሪ ነበሩ፣**
- **ደ/ር አብይ አህመድ ለሀገሩ ሂይወቱን አሳልፎ የሰጡ ሰው ናቸው፣**
- **ከሁሉም በላይ ደ/ር አብይ አህመድ የሁለት ብሄሮች ውጤት ናቸው፡፡**

ስለዚህ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም፡፡

የትግራይ ህዝብ እርግጥ ነው በተለያዩ ሰልፎች የተንፀባረቁ በተለይም በወጣቱ በኩል የሚታዩ ነገሮች ስጋት ሊያድርበት ይችላል፡፡ይህ ወጣት እኮ እንደው የአንድ አንድ ሰው መጠቀሚያ ሁኖ ተነፈሰ እንጂ እውነታው ራሱ የትግራይ ሰው ሊሆን ይችላል፣ ወይ ሚስቱ የትግራይ ሰው ልትሆን ትችላለች ግፋ ቢል ደግሞ ጓደኞቹ የትግራይ ተወላጆች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሰልፉ ላይ ያብዳሉ እንጂ በተጨባጭ ሰው ሲበተን ግን እውነታው ሌላ ነው፡፡

**<u>ስለዚህ ሁለት ነገር በዋነኝነት በትግራይም ሆነ እንደ ሀገር በሌሎች ብሄረሰብ ብሎም በመሪው መደረግ አለበት፡፡</u>**



ለማንኛውም አስተያየት በአዲሚኑ ኢሜል መስጠት ይቻላል፡

**በትግራይ በኩል፤**

1. አሁን ያለው አመራር የትግራይ ህዝብ ፍሬ ነው ስለዚህ ደ/ር አብይ አህመድ የትግራይ ህዝብ ተጋድሎ ውጤት ወይም ልጅ ነው፡፡ልጅ ደግሞ ሲያጠፉ እንመክረዋለን ብሎም እንቆነጥተዋለን እንጂ ከአካለችን አንለየውም ፣ አንጥለውም ፤ ብንጠላው እንኳን ተመልሶ ልባችን ይራራል፡፡
2. ህወሓት እና የትግራይ ክልል በየወረዳው ያለው አመራር ሙሉ ለሙሉ በአዲስ ወጣት ሃይል ይተካ፡፡ ነባር አመራሮች በክብረ ከፓርቲው አመራር ይሰነበቱ በመጨረሻም ደ/ር አብይ አህመድ የሚደግፍ ሰልፍ እና መግለጫ ይጠራ፣ ይሰጥ ፤ ከሁሉም በላይ ህዝብ መሳሪያ እስካላነሳ ድረስ ሰላማዊ ስልፍ እንደፈለገው እንድያደርግ መፍቀድ፡፡

**በሌላው ብሄረሰብ በኩል፡-**

1. የትግራይ ህዝብ ለከፈለው መስዋዕትነት የምስጋና ስላማዊ ሰልፍ ይውጣ በፍፁም ፍቅር ጥላቻን አስወግዶ ሰላማዊ ሰልፍ ይወጣ፡፡
2. በኢትዮጵያውነት ጠለቅ ያለ ስሜት ወደ ኃላ የምናይበት ሳይሆን ወደ ፊት የምንደመርበት አመለካከት እንድናሳደግ በአመለካከት መለወጥ ፡፡

**በመሪው ደ/ር አብይ አህመድ በኩል**

1. ስልጣን በብሄር እና በትውውቅ እንዳይሆን የእውነት ለውጥ ማምጣት፤
2. ለኢትዮጵያ የሚበጁ አማራጮት እንዲነሱ የግድ ደጋፊ ካልሆኑ ሳይሆን አማራጮች ነፃነታቸውን መስጠት፣ብሄር ከብሄር የሚያጣሉ ነገሮች ማጥፋት እና አጀንዳው ከህወሓት ተኮር ወደ ልማት ተኮር እንዲለወጥ ማድረግ፡፡

እኔ በግሌ ከላይ ያሉ ነገሮች **ያለ ጥላቻ በፍቅር መንገድ ብቻ** በአጭር ጊዜ ብንተገብር እውነት የምንወዳት ኢ/ያ ፣ ለመኖር የምንጋጓት አገር እንድትፈጠር መሰረት ይሆናሉ ብየ ስላሰብኳቸው ሁሉም ባለስልጣን ይህንን የማንበብ ዕድል ያለው ፤ **ሀሳቡን በፍቅር ወስደን** በመስራት ህዝቡ ተግባሩን በመውሰድ አንድ ስንሆን አጀንዳው **ከዘር ጥላቻ ዘመቻ ወደ ድህነት ማጥፋት ዘመቻ እንገባለን፡፡**



ለማንኛውም አስተያየት በአዲሚኑ ኢሜል መስጠት ይቻላል፡